# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE TWENTY: ምን ጉድ ነው የሰራሁት?

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE ONE: ምህረት REFLECTS ON HAVING SEX FOR THE FIRST TIME**

- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE TWO: ንጉሴ GETS READY FOR SCHOOL**

- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- **ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**SCENE THREE: ቅዱስ AND ብሩክ BEGIN THEIR JOURNEY HOME**

- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ብሩክ (M, 8)**
- **አቶ ደንበል (M, 40)**

## SCENE FOUR: EXAM TIME FOR ምህረት ’S CLASS

- ትዕግስት (F, 15)
- ምህረት (F, 15)
- ንጉሴ (M, 16)
- ዳንኤል (M, 16)
- ርዕሰ መምህርት ሰብለ ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)
- GROUP OF STUDENTS (M/F, 15)

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" የተሰኘው ድራማ 20 ኛ ክፍል ነው። የዛሬው ጭውውት «ምን ጉድ ነው የሰራሁት? » የሚል ርዕስ ይዟል። እስቲ ለመነሻ እንዲሆነን ሰሞኑን የሆነውን መለስ ብለን እንቃኝ።

ወ/ሮ ለምለም ወላጆቻቸው ሳያውቁ የምህረትን ሁለት መንታ ወንድሞች ብሩክን እና ቅዱስን በአንድ የማዕድን ማውጫ ሲያሰሩ በመቆየታቸው ልጆቹ ጠፍተው አመንገድ ዳር ለልመና ተዳርገዋል። ኋላም ጓዳና ያገኛቸው ሰው እንደሚረዳቸው ነግሯቸዋል። : **(KW BEGIN)**

2. ብሩክ **(EPISODE 19, LINE 20):** "እርዱን እባካችሁ። ወደ ቤታችን የምንመለስበት ገንዘብ ስጡን።"

3. አቶ ደንበል **(41):** "ማልቀስህን አቁም ልጄ። 35) የከባድ መኪና ሹፌር ነኝ። ታዲንካም መንገዴ ላይ ነው።. (…)ካሲምባ ድረስ አደርሳችኋለሁ።"

**(KW END)**

ብሩክ እና ቅዱስ በስተመጨረሻ ከወጃጆቻቸው ጋ ይቀላቀሉ ይሆን? ንጉሴስ? የአባቱን መኪና ሰርቆ አንዲት መንገደኛ ከገጨ በኋላ ምን ይገጥመው ይሆን?

**4. (EP 19, 71) SFX: SOMEONE BEING SLAPPED**

5. አቶ ጃለታ **(74):** "ምን አባህ ስታስብ ነው ? እእእ ንጉሴ !! ሴትየዋን እኮ ልትገድላት ትችል ነበር።"

   **(76)** "ንጉሴ ፤ አሁን ወደ ክፍልህ ግባ እና በደንብ አስብበት። "

እናስ ንጉሴ ጥፋቱን እንዴት ይቋቋመዋል። መልሱን ኋላ ላይ እንደርስበታለን። በመጀመሪያ ግን ምህረትን ታስታውሷታላችሁ አይደል? ዳንኤል ጋ ያልታሰበ ጉብኝት አድርጋለች።

**6. SFX: DOOR SLOWLY BEING OPENED (EP 19, 99)**

7. ዳንኤል **(98):** "ምህረት ? በህልሜ ነው በውኔ?"

8. ምህረት **(104):** "ዳንኤል … ስለጠየከኝ ነገር….እያሰብኩበት ነበር። **(114)** "ለአንተ ክብረ ንፅህናዬን ለመስጠት ዝግጁ ነኝ።

እንግዲህ ምህረት ከጋብቻ በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት ላለመፈፀም የነበራት አቋም ተለውጧል። ታድያ በመጨረሻ ፀፀት ውስጥ ትገባ ይሆን? በሚቀጥለው ማለዳ ይቿት አቤቷ ውስጥ። …

## <u>SCENE ONE: ምህረት REFLECTS ON HAVING SEX FOR THE FIRST TIME</u>

**9. SFX: MORNING ATMO (LIGHT TRAFFIC, BIRDS)**

**10. SFX:** ምህረት **YAWNS**

11. ምህረት**:** **(tired voice)** እፍፍ… እንዴት… ደክሞኛል… **(remembers)** ወይ ጉዴ!
    ምን ጉድ ነው የሰራሁት?

**12. SFX: BLANKETS PULLED OVER HEAD**

**13.** ምህረት: **(deep in thought, full of regret)** ድንግልናዬን አጥቻለሁ። ከአሁን በኋላ ጨዋ ልጅ አይደለሁም። … ትዕግስት የበለጠ ሴትነት ይሰማሻል ብላኝ ነበር።… ታድያ ይሰማኛል? አሁን የተለየ ነገር አለው? እእ… ይልቁንስ… ጥፋተኝነት … እና ሀፍረት ነው የሚሰማኝ። ግን ለምን? ዳንኤልን እወደዋለሁ። … እረዥም ቁመና፣ ውበት እና ገንዘብ አለው።… ከላቦሪያ ነው የመጣው። በዛ ላይ እሱ ብቻ ነው ብሶቴን የሚረዳኝ። ስለዚህ ከእሱ ጋ መተኛቴ ልክ ነበር…አልነበረም እንዴ?

**14. SFX: BEDCLOTHES RUSTLING**

**15.** ምህረት: **(still deep in thought)** ወይ ጉዴ! ወላጆቼ ለውጤን ያስተውሉ ይሆን እንዴ? ወይንም ደግሞ አሁን ከማሳየው ጠባይ አንፃር ለውጥ እንዳለኝ ይነግሩኝ ይሆን? የክፍሌ ጓደኞችስ ቢሆኑ?

**16. SFX: SQUEAKING SOUND FROM BED AS SHE GETS UP**

**17. SFX: FOOTSTEPS WALKING**

**18.** ምህረት : **(panic)** ወይኔ ጉዴ - እንዴት ረፍዷል። ፈተና እንዳያመልጠኝ መፍጠን አለብኝ።

**19. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE TWO: ንጉሴ GETS READY FOR SCHOOL</u>**

**20. SFX: BRUSHING OF TEETH**

**21. SFX: GURGLING OF WATER AND SPITTING OUT**

**22.** አቶ ጃለታ : የፈጣሪ ያለ፤ ንጉሴ ምን እያደረገ ይሆን? ስራ ደግሞ ረፍዶብኛል። እዛው በክፍሉ ከተዘጋ ዘመናት አለፉ አይደል እንዴ።

**23.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : **(hits back)** አንተ ራስህ አይደለህ ከክፍልህ እንዳትወጣ ያልከው። እስቲ ልሂድና ልየው።

**24. SFX: FOOTSTEPS WALKING**

**25. SFX: GENTLE KNOCK ON DOOR**

**26.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : ንጉሴ የኔ ልጅ... አባትህ ትምህርት ቤት ያደርስሀል።

**SILENCE**

**27.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : ንጉሴ በል ተነሳ ፤ ፈጠን በል። ከገሀዱ አለም ተደብቀህ እስከመቼ ትኖራለህ። **(short pause)** ያልታሰበ አደጋ ነበር። ይህ ያለ ነገር ነው። በማንም ላይ ሊደርስ ይችላል። አባትህ ላይም ቢሆን።

**KW BEGIN**

**28.** አቶ ጃለታ: **(far away)** ይህንን በኔ ላይ አትለድፊ! እኔ የ16 አመት ልጅ ሳለሁ። ከወላጆቼ የመኪና ቁልፍ አልሰረቅኩም ነበር።

**29.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : **(sarcastic whisper)** ወላጆችህ ኖረቸው የሚያውቀው ቢስክሌት ብቻ ስለነበረ ነዋ።

**30.** አቶ ጃለታ : ቢሆንስ። ምንም ይኖራቸው ምን እንኳን ልንነዳ ለመንካት እንኳን የተከለከልነውን አንነካም ነበር።

**31.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : **(whispers)** ጃለታ ልጃችንን ለመርዳት ስሞክር ምናለበት ትንሽ እንኳን ድጋፍ ሰጪ ብትሆን።

**KW END**

**32.** ንጉሴ : **(from inside)** ሴትየዋን ገድያት ነበር ማለት ይቻላል። በላይዋ ላይ እኮ ነው የሄድኩት። ምስሉ ከጭንቅላቴ ሊወጣ አልቻለም።

**33.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(comforting)** ወይጉድ ንጉሴ ! አይዞህ። ማንም አልሞተም። እንደሱ አታስብ። አሁን ስለዚህ በተዘጋ በር ነው ማውራት ያለብን? ቆይ ደግሞ ... ምንድን ነው የሚሸተኝ ንጉሴ ! ክፈተው ልግባ።

**34. SFX: DOOR BEING OPENED**

**35.** ወ/ሮ ዘውዲቱ: **(shocked)** ምን እየሰራህ ነው አንተ? **(shouting)** ጃለታ ይህን ናና ራስህ ተመልከት።

**36. SFX: FOOTSTEPS WALKING QUICKLY**

**37.** አቶ ጃለታ: ይህ የጤና አይደለም -- **(stops midway)** አታደርገውም ንጉሴ ፤ ለመሆኑ ከመቼ ጀምሮ ነው …? **(furious)** በል ቶሎ ይህንን ሲጋራ አሁኑኑ ከአፍህ ውስጥ አውጣ ።

**38.** ንጉሴ : **(softly)** ይህን ያህል መጮህ አያስፈልግህም አባዬ። በደንብ ትሰማኛለህ።

**39.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : አንተ እንደምታደርግ አድርገው ጃለታ ። እኔ ይህን ማየት አልችልም።

**40.** አቶ ጃለታ : አሁን ረፍዷል ንጉሴ ። ደብተሮችህን ያዝ እና ና ወዲህ ውጣ። ስለዚህ ማታ እናወራለን።

**41.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : ፖሊስ ጣቢያ ደረስ ማለትህን እንዳትረሳ። ሙላቱን ማሰር አለባቸው። መኪናዬን እፈልጋታለሁ።

**42.** አቶ ጃለታ : **(takes deep breath)** አንቺ ደግሞ ፤ ልጃችን አሁን ሲጋራ ሲያጨስ ደርሰንበት እያለ ያንቺ ልብ ያለው የተሰረቀው መኪናሽ ላይ ነው።

**43.** ንጉሴ: **(gently)** አቶ ሙላቱ?በጭራሽ። ልክ አትመስሉኝም። ለምንድን ነው እሳቸውን ብቻ የምትጠረጥሩት። የምህረት አባት ከስርቆቱ ጋ ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም።

**44.** አቶ ጃለታ : **(orders)** አንተ ደግሞ አፍህን ዝጋ። የት የምታውቀውን ነው። ከአሁን በኃላ አንዲት ነገር ትንፍሽ ብትል ሲጋራው ከውስጥህ እስኪወጣ ድረስ ነው የምዶልዝህ። አሁን ና ውጣ።

**45. SFX: SOMEONE BEING PUSHED AND FALLING DOWN**

**46.** ወ/ሮ ዘውዲቱ : **(screaming)** ጃለታ በቃህ። ትጎዳዋለህ።

**47. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE THREE: ቅዱስ AND ብሩክ BEGIN THEIR JOURNEY HOME</u>**

**48. SFX: HEAVY TRUCK ENGINE BEING TURNED ON**

**49.** አቶ ደንበል : በሉ አሁን በደንብ አድምጡኝ። እናንተ ሁለት ልጆች። ስማቹህ ማን ነበር?

**50.** ቅዱስ : **(at the same time)** ቅዱስ

**51.** ብሩክ : **(at the same time)** ብሩክ

**52.** አቶ ደንበል : ቅዱስ እና ብሩክ ። ትክክል። ይቅርታ ስም አያዝልኝም። በሉ ልጆች ጉዞዋችንን እንጀምር። አሁን ከኦአንጎ ለቀን ወደ ኪሲምባ እንሄዳለን።

**53.** ቅዱስ : **(interrupts** አቶ ደንበል **, excited)** በጣም አሪፍ። እማዬን እና አባዬን፣ ምህረትንና ታንዲካ ያሉ ጓደኞቻችንን በሙሉ እናገኛቸዋለን ማለት ነው።

**54.** ብሩክ : ዝም በል ቅዱስ ። አቶ ደንበል የሚሉትን እንስማ!

**55.** አቶ ደንበል : ምንም አይደል ብሩክ ። ቤተሰቦቻችሁን ለማየት መቸኮላችሁ ይገባኛል። ግን አንድ ነገር ላስጠንቅቃችሁ፤ መንገዳችን በጣም ረዥም ነው። በዚህ መኪና በፍጥነት ልነዳ አልችልም። ዕድለኞች ከሆንን ነገ እንደርሳለን። ዝናብ ከጣለ ግን መንገዱ ስለሚያስቸግር ነገም ላንደርስ እንችላለን።

**56.** ብሩክ : አቋራጭ መንገድ የለም? በምንኖርበት በታንዲካ ጎስቋላ መንደር ሁልጊዜ አቋራጭ መንገዶች አሉ።

**57.** አቶ ደንበል : (laughing) የለም ብሩክ ። ቢኖር እኔም ደስ ባለኝ ነበር። ያለው መንገድ አንድ ብቻ ነው። በነገራችን ላይ ማንም ሰው ቢጠይቃችሁ አባታችን ነው ነው የምትሉት።

**58.** ቅዱስ : ግን እርሶ እኮ አባታችን አይደሉም።

**59.** አቶ ደንበል : ጣጣ እንዳይፈጠርብን ነው። ልጆቹ አለመሆናችሁን ካወቁ፤ የሰረቅኋችሁ ነው የሚመስላቸው። ከዚያም የሚከሰተውን ጣጣ አስቡት።

**60.** ብሩክ : ወደዚህ መልሰው ይልኩናል?

**61.** አቶ ደንበል : ትክክል! ወደዚህ ይመልሷችኋል። ይህ ብቻ አይደለም እናንተን እንደጠለፍኳችሁ አድርገው ያስሩኛል። ስለዚህ አስታውሱ በዚህ ጉዞ አባታችሁ ነኝ። ታንዲካ ስንደርስ አባታችሁ መባሌ ያበቃል እሺ።?

**62.** ብሩክ & ቅዱስ : እሺ።

**KW BEGIN**

**63.** አቶ ደንበል : ለመንገዳችን የሚበቃንን ምግብ እና መጠጥ ገዝቻለሁ።

**64.** ቅዱስ : ሽንት ቤት መሄድ ስንፈልግስ?

**65.** ብሩክ : ቅዱስ፤ መኪና ውስጥ አትሽናም።

**66.** አቶ ደንበል : የለም የለም። መፀዳዳት ስትፈልጉ መኪናውን አቆምና ወደ ቁጥቋጦው ገብታችሁ ትፀዳዳላችሁ።

**67.** ቅዱስ : እንዴ እዚያ አንበሳ ቢኖርስ?

**68.** ብሩክ: (worn out by questions) ቅዱስ ! በቃህ። አስር ሺ ነገር አትጠይቅ።

**69.** አቶ ደንበል **:** አይዞህ ቅዱስ። የዱር አራዊት ወደሰፈሩበት ጫካ አደለለም የምንሄደው። ምንም አንበሳ የሚባል ነገር የለም፤ አይዞህ ። ቅርብ ሆኜ እጠብቅሀለሁ። መተኛት ከፈለጋችሁ ፤ አልጋው ከመቀመጫችሁ በላይ ነው። ሁሉም ነገሮች አሉን ግልፅ ነው?

**70.** ብሩክ **:** አዎ!

**71.** አቶ ደንበል **:** ወይንስ ሌላ ጥያቄ አላችሁ?

**72.** ቅዱስ /ብሩክ **:** የለንም።

**KW END**

**73.** አቶ ደንበል **:** በሉ እንግዲህ ጉዞዋችንን እንቀጥል።...

**74. SFX: TRUCK ACCELERATES AND DRIVES OFF**

**75. MUSIC INTERLUDE**

**SCENE FOUR: EXAM TIME FOR ምህረት ’S CLASS**

**76. SFX: CLASSROOM ATMO, STUDENTS MURMURING**

**77.** ትዕግስት**:** **(curious)** ምህረት፤ ዛሬ ምን ሆነሻል? በአውቶቢስ ፌርማታው ቆሜ ጠበኩሽ እና ስትቀሪ ጊዜ ትቼሽ መጣሁ። ...

**78.** ምህረት **:** ታሪኩ ረዥም ነው ባክሽ። እንኳንም ብቻ በሰዓቱ ደረስኩ።

**79.** ትዕግስት**:** **(whispers)** ምህረት እስቲ ገምች?ትናንት ብታይ ከጓደኛዬ ጋ እንዴት ጥሩ ጊዜ አሳለፍን መሰለሽ። **(laughs cheekily)** ታውቂዋለሽ አይደል? ያንን የታክሲ ረዳቱን አሪፍ ልጅ። ...

**80.** ምህረት : አዎ አውቀዋለሁ፤ ትዕግስት። ስለዚህ በኋላ ልናወራ እንችላለን? አሁን የባዮሎጂ ፈተናችን ላይ እናተኩር። በዛ ላይ መምህርቷ በማንኛቸውም ጊዜ ሊመጡ ይችላሉ። አሁን አንዴ የመጨረሻ ክለሳ ላድርግ።

**81.** ትዕግስት: **(bored)** ኡፍ አንቺ ደግሞ … ሁሌ እንዳጠናሽ..

**82. SFX: PAGES OF A BOOK BEING TURNED**

**83.** ንጉሴ : **(clears throat)** ታድያስ ምህረት ።

**84.** ትዕግስት: **(sarcastic)** አረ! እኔ አልታይህም እንዴ? ከምህረት ጎን እኮ ነው የተቀመጥኩት። ግን ማንም ሊያየኝ አልቻለም።

**85.** ምህረት: አይቶሻል ትዕግስት **(sighs)** እ ንጉሴ ምንድን ነው?

**86.** ንጉሴ : ምንም… ይቺን - ደብዳቤ ውሰጂና ለብቻሽ ስትሆኚ አንብቢያት።

**87.** ምህረት : ንጉሴ ስንት ጊዜ ልንገርህ። እኔ ከ--

**88.** ንጉሴ : እንኪ ውሰጂ እና አንብቢው አባክሽ። አስቸኳይ ነው። የምችለውን በሙሉ አድርጌያለሁ።

**89.** ትዕግስት: **(acting concerned)** አረ አረ! ምህረት ። ንጉሴ ከህይወቱ በላይ የሚሳሳላት ፍቅሩ ክዳው ሌላ በመምረጧ፤ እራሱን ለማጥፋት የሚያቅድ ይመስለል። ምህረት ከክፍል ሳይወጣ ደብዳቤውን ብታነቢው ይሻልሻል! **(laughs)**

**90.** ንጉሴ : **(angrily)** ትዕግስት ፤ ይህ አይመለከትሽም። አርፈሽ ተቀመጭ።

**91.** ምህረት : እሺ አነበዋለሁ። ግን ከፈተና በኋላ። አሁን ማጥናት --

**92.** ንጉሴ : አሁን ብታነቢው ይሻላል። በኋላ ይዘገይ ይሆናል።

**93.** ትዕግስት : አ አ ። መርዙን አስቀድሞ ሳይወስድ አይቀርም።

**94.** ንጉሴ : **(furious)** ከአሁን በኋላ አንዲት ነገር ብትይ ትዕግስት፤ አጠናግርሻለሁ። ምህረት - ስለ አባትሽ ነው።

**95.** ምህረት : እሺ በቃ ተረጋጋ። አሁኑኑ አነበዋለሁ።

**96. SFX: PAPER BEING UNFOLDED**

**97.** ምህረት: **(shocked)** ምን? እየቀለድክ ነው? ንጉሴ፤ ምን እያልክ ነው? በፍፁም ይህ እውነት ሊሆን አይችልም።

**98. SFX: FOOTSTEPS APPROACHING**

**99.** ዳንኤል : ምንድን ነው ችግር አለ እንዴ ምህረት ?

**100.** ንጉሴ : ችግሩ ሁልጊዜ አንተው ነህ ዳንኤል ።

**101. SFX: MURMURS AND GRUMBLES FROM STUDENTS**

**102. SFX: HIGH-HEELED FOOTSTEPS**

**103.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : ዳንኤል እና ንጉሴ፤ ወደ መቀመጫችሁ ተመለሱ። ሁላችሁም አሁን ደብተራችሁን ከደኑና ከጠረቤዛችሁ ጉን አድርጉ።

**104. SFX: BOOKS BEING CLOSED AND DESKS OPENED AND SHUT**

**105.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : በሉ አሁን ከመጀመራችን በፊት ፤ ይገባኛል አንዳንዶቻችሁ ከደብተር እና መፅሀፋታችሁ ልትኮርጁ እንደምትሞክሩ ፤ ግን ይህን ስታደርጉ ብይዛችሁ ምን አለች በሉ ከፈተና ነው የማሰናብታችሁ። ዜሮ ነው የምታገኙት ይህንንም ለወላጆቻችሁ አሳውቃለሁ። ግልፅ ነው። እኔን አታልላለሁ ብላችሁ ከማሰባችሁ በፊት ሁለት ጊዜ አስቡበት። አሁን የፈተናውን ወረቀት አድላለሁ። እኔ ጀምሩ እስክላችሁ ድረት ወረቀቱን መግለጥ የለም።

**106. SFX: PAPER PUT ON THE TABLE**

## 107. MUSIC INTERLUDE

## 108. OUTRO - NARRATOR:

ምህረት  እና የክፍሏ ልጆች ፈተና ለመፃፍ በዝግጅት ላይ ሳሉ፤ እኛም 20ኛውን የጭውውት ክፍል እናጠናቅቃለን። ንጉሴ ለምህረት ምን ይሆን የገፈላት?  ምህረት , ንጉሴ , ዳንኤል  እና  ትዕግስት ፈተናውን በደንብ ይሰሩ ይሆን ? ቅዱስ  እና ብሩክንም አስታውሱ፤  ወደ ታንዷካ ጉዞ ጀምረዋል። በሰላም ይደርሱ ይሆን? ይህንን እና ሌሎችንም በሚቀጥለው ክፍል ይዘን እንቀርባለን። ይህንን ክፍል ደግመው መስማት ከፈለጉ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችንን ይጎብኙ፤ አልያም በፌስቡክ አድራሻችን ላይ ይከታተሉ። እስከሚቀጥለዉ ጊዜ ጤና ይስጥልን።